ወርኃዊ ጥንቅር ቁጥር 1
መጋቢት 2017 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ


## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል


+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


፮ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመጋቢት ወር አበይት ክንውኖች ........ 1

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ........ 2

የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች ........ 4

የውክልና ሥራ ........ 6

የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........ 7

የፓርላማ ዲፕሎማሲ ........ 11

የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ ........ 12

ምክረ-ሐሳቦች ........ 17

ይኽ ቀዳሚው የመጋቢት ወር የእንደራሴ ዕትም፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ እንደራሴዎች ካከናወኗቸው አበይት ተግባራት መካከል፣ የምክር ቤቱ ተልዕኮዎች የሆኑትን አራት ዋንኛ ጉዳዮችን አካቷል። እነዚህም፣ ሕግ ማውጣት፣ የተመራጭነት ውክልና፣ የአሥፈጻሚ አካላት ቁጥጥር እና የፓርላማ ዲፕሎማሲ ናቸው። ከአሥፈጻሚ አካላት ቁጥጥር ተግባራት ውስጥ የሚካተተው፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትርሚ ዐቢይ አሕመድ፣ የፌዴራል መንግሥቱንት የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት አፈፃፀምን መነሻ በማድረግ፣ እንደራሴዎቹ ላነሷቸው ጥያቄዎች መልስ እና ማብራሪያ መስጠታቸው ሲሆን፣ ይኽም የመጋቢት ወር ተጠቃሽ ክንውን ነው። ከዚኽ የርዕሰ-መንግሥቱ ፖለቲካል-ኢኮኖሚ እና የውጪ ጉዳይ ነክ ማብራሪያዎች በተጨማሪም፣ ይኽ የመጀመሪያ ዕትማችን፣ እንደራሴዎች ያጸደቋቸውን ሕግጋት፣ የፈጸሟቸውን የእንደራሴነት የውክልና ተግባራት፣ ያደመጧቸውን የተቋማት ሪፖርቶችና የመስክ ጉብኝቶች፣ እንዲኹም የፈጸሟቸውን የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን አሰባስቦ እና በተመረጡት አንኳር ጉዳዮች ላይ የብሪጅን ዳሰሳዊ ምልከታ አካቶ በዚኽ መልክ አቅርቧል።

# 6ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመጋቢት ወር አበይት ክንውኖች

**4ኛ ዓመት**

**መጋቢት 04**

**19ኛ መደበኛ ስብሰባ**

የኢትዮጵያ የተመሰከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ማጽደቅ።

**መጋቢት 09**

**20ኛ መደበኛ ስብሰባ**

የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት።

**መጋቢት 11**

**21ኛ መደበኛ ስብሰባ**

በፌዴራል መንግስት የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የአፈፃፀምን መነሻ በማድረግ ከምክር ቤት አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ምላሽና ማብራሪያ።

**መጋቢት 23**

**22ኛ መደበኛ ስብሰባ**

የፌደራል መንግስት በክልሎች ጣልቃ የሚገባበትን ስርዓት ለመደንገግ የወጣ ማሻሻያ አዋጅ ላይ ተወያይቶ አዋጁን ማጽደቅ።

**4ኛ ዓመት**

# ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ

ማዕከላዊ መንግሥቱ ኃይል የሚጠቀመው በምን ኹኔታ እና ምን ሲገጥመው ነው? የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ጉዳይስ? ኢኮኖሚውስ እንዴት ሰንብቷል? በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛው ዙር፣ 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን፣ 21ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት የአገሪቷ ርዕሰ-መንግሥት፣ ይኽን መሰሉቹን ጥያቄዎች ጨምሮ፣ በዛ ባሉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ምላሾችን ሰጥተዋል፤ አኹናዊ የመንግሥታቸውን አቋሞችም አስረድተዋል።





ጠቅላይ ሚንስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ

## ኢኮኖሚው እንዴት ሰነበተ?

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ በሠጡት ማብራሪያ፣ መንግስት በቀጣዬቹ ዐሥር ዓመታት የሚተገበር የልማት ዕቅድ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል። ከዚኽ ባለፈም፣ የዐሥር ዓመቱን መሪ ዕቅድ መነሻ ያደረገ የአምስት ዓመት እና የአንድ ዓመት የተግባር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም አብራርተዋል። እንደራሴዎቹ በአገሪቷ ዐቢይ ኢኮኖሚ ዙሪያ ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል፣ በአምራች ዘርፉ ያለውን የጥሬ ዕቃ የአቅርቦት ችግሮች፣ የዐሥር ዓመቱ ዕቅድ ከየት ወዴትነት፣ የነዳጅ ድጎማ እና ሕገ-ወጥ ሽያጭ፣ ተጀምረው የተጓተቱ አገራዊ ፕሮጀክቶች እንዲኹም የአፈር ማዳበሪያ ሥርጭት መዘግየትን የተመለከቱት ጥያቄዎች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። ለእነህ መሰሎቹ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩም፣ ባለፉት ስምንት ወራት በዋና ዋና የዐቢይ ኢኮኖሚ አመላካቾች ታላላቅ ስኬቶች ተመዝግበዋል ብለዋል። በተያዘው የበጀት ዓመቱ ቀሪ ወራት ይኽን ስኬት ማጠናከር ከተቻለ፣ ኢትዮጵያ ከ8 ነጥብ 4 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ እድገት ታስመዘግባለች ሲሉም ገልጸዋል። ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮች ቢያጋጥሙም፣ ባለፈው ዓመት ኢትዮጵያ 8 ነጥብ 1 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገቧን ያነሱት ዐቢይ፣ 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የዕዳ ሽግሽግ መገኘቱንም ተናግረዋል። በቀደመው ሐምሌ ወር 2016 ዓ.ም. ከተጀመረው ዐቢይ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ በነበረው ድርድር፣ የዕዳ ሽግሽግ ለማድረግ ሲሰራ መቆየቱን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኢትዮጵያ አቋም ዕዳ እንዲሰረዝ ማድረግ መኾኑንም ሲናገሩ ተደምጠዋል። አኹን ኢትዮጵያ እየሞከረች ያለችው ከጥቅል አገራዊ ምርቷ ሰባት በመቶ ገደማ ገቢ ለማስገባት መኾኑንም የጠቀሱት ጠቅላዩ፣ በሚቀጥሉት አራት ወራት አኹን ባለው ሂደት ከተኬደ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ስኬት ይመዘገባል ብለዋል።



የዋጋ ንረትን እና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች መኾኑን ሲናገሩ የተደመጡት እንደራሴዎቹም፣ የምግብ ዋጋ ግሽበት መቀነሱን አስመልክቶ ሪፖርት ቢቀርብም፣ ሪፖርቱ ከእውነታው ጋር ምን ያክል የተቀራራበ ነው? ሲሉም ጥያቄያቸውን ወርውረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምላሻቸው፣ የዋጋ ንረትን ለማሻሻል እየተሠራ መኾኑን አንስተው፣ የዋጋ ግሽበትን ግን መቀነስ መቻሉን ተናግረዋል፤ የምርት መጨመር፣ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ እና ሌሎች ሥራዎች የዋጋ ንረቱን ቀንሰውታል ሲሉም ተሰምተዋል።

| ባለፉት ስምንት ወራት | |
|---|---|
| የኢኮኖሚ እድገት ትንበያ | > 8.4%) |
| ለነዳጅ እና የአፈር ማዳበሪያ ድጎማ | 156 ቢሊዮን ብር |
| የአገር ውስጥ ገቢ | > 580 ቢሊዮን ብር |
| የዕዳ ሽግሽግ | 3.5 ቢሊዮን ዶላር |
| ለውጭ ገበያ | 4.5 ቢሊዮን ዶላር |
| የአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሥራ ስምሪት | > 3 ሚሊዮን |

## ጠቅላይ ሚንስትሩ የታጠቁ ኃይሎችን፣ “አያዋጣም ተዉት” ብለዋል።

ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን በውይይት እና በድርድር የመፍታት ልምምዳችን አነስተኛ ነው ሲሉ የተደመጡት እንደራሴዎቹ፣ መንግስት ፖለቲካዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያብራራ ጠይቀው ነበር፡፡ መንግስት ሰላምን ያስቀደመ እና ለሰላም የሚተጋ መሆን አለበት ሲሉ ምላሻቸውን የጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩም፣ መንግስት በብቸኝነት ኃይል የመጠቀም ሥልጣን ያለው በመሆኑ ዘላቂ ሰላምን እና ፍትሓዊነትን ለማረጋገጥ ወደ ግጭት ሊገባ እንደሚችል ተናግረዋል። መንግስት በብቸኝነት ኃይል የመጠቀም መብት ያለው አካል ስለኾነ ለዘላቂ ሰላም ሲል ይዋጋልም ብለዋል፡፡ ከተለያዩ ታጣቂዎች ጋር ይደረጋሉ ስለሚባሉ ድርድሮችም ሲያወሱ፣ መንግስታቸው ለሰላም እጁ የተዘረጋ መሆኑን በማንሳት፣ በድርድር እና በሰለጠነ መንገድ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ሁሌም ቢሆን ዝግጁ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

የምንዋጋቸው መድኃኒት አውጥተው የሚደፉ፤ ማዳበሪያ እንዳይደርስ የሚያደርጉ፣ ነገር ግን ለሕዝብ እንታገላለን ባይ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለሕዝባቸው ትምህርት ምን ያደርግላቸዋል ብለው የሚያስቡ ናቸውም ሲሉ ተሰምተዋል። ነውጠኛ ነፃ አውጭ ነን ባዮች መጀመሪያ ተጎጂ የሚያደርጉት የራሳቸውን ሕዝብ ነው ያሉት ዐቢይ፣ ስለምንታገልልህ እንገድለሃለን፤ እኛ ታጋዮች ስለኾን የምናደርገው ሁሉ ትክክል ነው ይሉታል ሲሉም በዚኹ ማብራሪያቸው ላይ አንስተዋል። ጦርነት እንደማይጠቅም በወሬ ሳይኾን በተግባር አይተነዋል ነው ያሉት ጠቅላዩ፣ መከላከያ ተወጥሯል ጦርነት እናንሳ የሚሉ አሉ፤ ምክሬ ግን አያዋጣም፣ አይኾንም ተዉት የሚል ነው ሲሉም ተናግረዋል።

## የቀይ ባሕር ጉዳይ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ፣ መንግስታቸው በባሕር በር ጉዳይ ላይ ያለውን አኹናዊ አቋም ባብራሩበት በዚያ የእንደራሴዎቹ ውሎ፣ የቀይ ባሕር ፍላጎታችን ከሶማሊያ፣ ጅቡቲ እና ኤርትራ ጋር የሚያዋጋ መሆን የለበትም ብለዋል።፣ የቀይ ባሕር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው ሲሉ በድጋሚ ለምክር ቤቱ አባላት የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ 130 ሚሊዮን ሕዝብ ተዘግቶበት እስር ቤት ውስጥ ሊኖር አይችልም ብለው ሲናገሩም ተደምጠዋል። በዚኽ ቀይ ባሕር ተኮር ማብራሪያቸው ኤርትራን ደጋግመው ያነሱት ዐቢይ፣ የኤርትራ ሕዝብ ወንድም፣ ምስኪን እና እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ለማደግ የሚፈልግ ሕዝብ ነው ሲሉ ገልጸው፤ ተባብረን መልማት እና መሥራት እንጂ አንዱ አንዱን መውጋት የእኛ እቅድ አይደለም ሲሉም አኹናዊውን የመንግስታቸውን አቋም ለእንደራሴዎቹ አጋርተዋቸዋል። በዚያ ማብራሪያቸውም፣ ኢትዮጵያ ለቀይ ባሕር ስትል ኤርትራን የመውረር ፍላጎት የላትም ሲሉም አበክረው ተናግረዋል። የባሕር በር ጥያቄን ማንሳት ነውርነቱ አቁሟል ሲሉ የተሰሙት ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ የዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ አቋምም በዓለም ላይ ትልቅ አገር ሆኖ የባሕር በር የሌለው የለምና፣ የባሕር በር የማግኘቱ ጉዳይ በሰጥቶ መቀበል መርህ ሊሆን ይገባል የሚል ነው ሲሉም ለምክር ቤት አብራርተዋል።

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች

በተጠቀሰው መጋቢት ወር፣ ምክር ቤቱ ኹለት አዋጆችን ያጸደቀ ሲሆን፣ አንድ ረቂቅ አዋጅን ለሚመለከተው የቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ ልኳል፤ ከዚኽ በተጨማሪ፣ ሦሥት የአስረጂ መድረኮችን በረቂቅ ሕጎቹ ላይ አከናውኗል፡፡



## የጸደቁ ሕጎች

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በወርሃ መጋቢት ካፀደቃቸው ሕግጋት አንዱ፣ የተመሠከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅን ነበር። በ19ኛው መደበኛ ስብሰባው፣ የቀረበለትን ይኽንኑ ረቂቅ የተመለከተው ምክር ቤቱ፣ አዋጁን በመርመር፣አዋጅ ቁጥር 1372/2017 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል፡፡ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ደሳለኝ ወዳጄም፣ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳቡን ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት፣ አዋጁ በኢትዮጵያ ዓለም ዓቀፍ የተመሠከረላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት አቅም የሚፈጥር መሆኑን አብራርተዋል፡፡ የሒሳብ ባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ በዘርፉ እየተከሰተ ያለውን የገንዘብ ብክነት ከማስቀረት ባለፈ፣ የሕዝብ እና የአገርን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችል ረቂቅ መሆኑንም ሰብሳቢው አስገንዝበዋል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ኢዮብ መኮንን በበኩላቸው፣ ረቂቅ አዋጁ ዓለም ዓቀፋዊ እና አህጉራዊ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ጠቁመው፣ የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ፣ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩ የሒሳብ አያያዝ፣ ኦዲት እና የፋይናንስ መረጃዎችን የማስተዋወቅ ሚናው ከፍ ያለ እንደሚሆን አብራርተዋል፡፡

በኹለተኛነትም ምክር ቤቱ፣ አኹን በሥራ ላይ ያለውን የፌዴራል መንግሥቱ በክልሎች ውስጥ ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ በሚል በ1995 ዓ.ም. የወጣውን አዋጅ አሻሽሏል። በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ ክዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ እና የፍትሕ ሚኒስትሯ ሃና አርያ ሥላሴ፣ አዋጁ እንዲሻሻል ያስፈለገባቸውን የተለያዩ ምክንያቶች ለእንደራሴዎቹ አብራርተዋል። ምክር ቤቱ፣ መጋቢት 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 22ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የቀረበለትን ይኽንኑ የማሻሻያ አዋጅ ያፀደቀው በኹለት ድምጸ-ተዐቅቦና በአብላጫ ድምጽ ሲሆን፤ ነባሩን አዋጅ ቁጥር 359/1995ን ተክቶ 'የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ ሻሻያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1373/2017'' በሚል አፅድቆታል። የአዋጁን የማሻሻያ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አሥተዳደርን እንደምሳሌ በማንሳት፣ የአሥተዳደሩ ዘመን በቀደመው አዋጅ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክልሉ ካለበት ነባራዊ ኹኔታ ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ በአዋጁ አተገባበር ወቅት ክፍተት ተፈጥሯል ሲሉ የማሻሻያውን አስፈላጊነት አብራርተዋል፡፡ (ስለዚኹ አዋጅ ዳሰሳዊ ምልክታችንንን ገጽ 12 ላይ ይመልከቱ)።

## ረቂቅ ሕጎች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ መጋቢት 9 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 20ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 16/2017ን፣ ለዝርዝር ዕይታ በሙሉ ድምጽ ለውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶቷል። በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌም፣ ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያም፣ የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የቅድመ-አደጋ፣ የአደጋ ወቅት እና ድህረ-አደጋ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የፌዴራል እና የክልል አሥተዳደር ተቋማት የውስጥ አቅም ለመገንባት[1] አዋጁ ማስፈለጉን አንስተዋል። ከዚያ ባለፈም፣ ቅጽበታዊ አደጋ ሲከሰት እና ከአቅም በላይ ሲሆንም የአስቸኳይ ጊዜ እወጃ ሥርዓት ከመዘርጋት አንስቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጭምር ይኸው ረቂቅ ማስፈለጉን ለምክር ቤቱ አባላት አስረድተዋል። እንደ ረቂቅ አዋጁ ማብራሪያም፣ በቅድመ አደጋ፣ አደጋ እና በድህረ-አደጋ ወቅቶች ለሚወሰዱ የአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ ምላሽ እና መልሶ ማቋቋም የሚሆን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ምላሽ ፈንድ ይቋቋማል። ፈንዱም ከሠራተኞች ደመወዝ ላይ ከሚቆረጥለት ገቢ በተጨማሪ ከባንኮች እና ከተለያዩ የፋይናንስ እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፣ ከፌዴራሉ መንግሥት፣ ከኹለቱ ከተማ አሥተዳደሮች እንዲኹም ከጠቅላላው ዓመታዊ በጀት በድርሻ እንደሚሰበሰብም ተብራርቷል፡፡[2]

## የአስረጂ መድረኮች

ምክር ቤቱ ባሳለፍነው መጋቢት ወር በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ እና የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ቲንክ ታንክ አልያም ጥናታዊ የፖሊሲ ግብዓት አውጪ ቡድን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብን ጨምሮ፣ ኹለት የአስረጂ መድረኮችን አካሂዷል፡፡

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ በሚል ስያሜ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ተከትሎም፣ የምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና የአካባቢ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ከተባሉ ባለድርሻዎች ጋር ሰፋ ያለ የአስረጂ መድረክን አካሄዷል። መጋቢት 15 ቀን በዋለው መድረክ ላይ የተገኙት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተሯ ሌሊሴ ነሜ፣ ረቂቅ አዋጁ የግል ዘርፉን ከትርፋማነት ጎን ለጎን የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ከመንግስት ጋር እንዲሠሩ ዕድል ይፈጥራል ሲሉ የአዋጁን አስፈላጊነት አብራርተዋል። ነባሩ አዋጅ(ቁጥር 513/1999) 18 ዓመታትን ያስቆጠረ እንደመሆኑ፣ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ለገጠሩ የማኅበረሰብ ክፍል ብዙ ትኩረት ያልሰጠ መሆኑንም ሌሊሴ ጨምረው አንስተዋል።[3]

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ መጋቢት 29 2017 ዓ.ም. ላይ ያካሄደው ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ቲንክ ታንክ ቡድን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብን የተመለከተው ነበር። የከተማ እና መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባዘጋጀው ይኸው የአስረጂ መድረክ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የዘርፉ ሙያተኞች ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸው ተገልጿል። ከዚኽ ባለፈም፣ የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታው የትም ጌታ አሥራት፣ በዚኽ ወቅት የኢትዮጵያን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ማነቆዎችን በመፍታት ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ ማሸጋገር እንደሚገባ ተናግረዋል። መንግስትም የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለማሳደግ የዘርፉን ሙያተኞች በማቀራረብ ለአገር የሚጠቅሙ ሐሳቦችን በጋራ ለማፍለቅ ዝግጁ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው ለመድረኩ ተሳታፊዎች ጨምረው አብራርተዋል። መድረኩን ያዘጋጀው የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ ከባለድርሻ አካላት አስተያየት በማሰባሰብ ለረቂቁ ግብዓት እንዲሆን ለከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር መሰጠቱን ጠቅሰዋል።

---

1 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መራ” https://www.hopr.gov.et/-/ምክር-ቤቱ-የኢትዮጵያ-የአደጋ-ስጋት-ስራ-አመራር-ረቂቅ-

2 ሪፖርተር “የመንግሥትና የግል ሠራተኞች ከደመወዛቸው ለአደጋ ሥጋት ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስገድድ ረቂቅ አዋጅ ቀረበ” https://www.ethiopianreporter.com/139426/

3 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ረቂቅ አዋጅ ላይ የአስረጂ መድረክ ተካሄደ”https://web.facebook.com/share/p/14tC8C6ZSd/

# የውክልና ሥራ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ እንደራሴዎች፣ ከሚጠበቁባቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል አንዱ የውክልና ሥራ ነው። እንደራሴዎቹም ወደ ‘ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን ማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን መስማት፣ በዓመት ኹለት ጊዜ የሚከውኑት ተግባር ነው። ከዚኽ አኳያም፣ የምክር ቤቱ አባላት ይኽንኑ የውክልና ሥራቸውን ከየካቲት ወር በመቀጠል በመጋቢት ወርም ከውነዋል።


በተጠቀሰው መጋቢት ወር ላይም፣ ከ40 በላይ የሚሆኑ የመራጭ -ተመራጭ መድረኮች ሲካሄዱ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሶማሌ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ውይይቶቹ የተካሄዱባቸው ክልሎች ነበሩ። በእነዚኽ ክልሎች በተካሄዱት ውይይቶችም፣ ሰፋ ያሉ አገራዊ እና አካባቢያዊ አጀንዳዎች በጥልቀት ተዳስሰዋል።

በእነዚያ መድረኮች ላይም በተደጋጋሚ ከተነሱት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል፣ የሴቶች ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች እና ሴቶች እና ሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ቀዳሚውን ስፍራ ይዘዋል፡፡ በኦሮሚያ/ ምዕራብ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ/፣ ወላይታ፣ አማራ/አዊ/ እና ዳውሮ ዞኖች በተካሄዱት ውይይቶች የሴቶችን ሕገ-መንግሥታዊ መብት እና ጥቅም ማስከበር፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ እንዲኹም ፆታ ተኮር ጥቃቶችን በጋራ መከላከል እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መግታት የሚሉት ተደጋግመው ከመራጮቹ በኩል የተነሱ ርዕሰ-ጉዳዮች ነበሩ። በተለይም ሴቶች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የመሠራታቸው አስፈላጊነት ላይ በውይይት መድረኮቹ ላይ ሲነሳ፣ ጉዳዩ በእንደራሴዎቹ በኩልም አጽንዖት ተሰጥቶበታል፡፡

በመጋቢቱ የእንደራሴዎቹ የውይይት መድረኮች ላይ፣ በኹለተኛነት ተደጋግመው ከተነሱት አገራዊ ጉዳዮች መካከል የሰላም እና የጸጥታ እንዲኹም የመሠረተ-ልማት ግንባታ መጓተቶች ቀዳሚዎቹ ሆነዋል። በኦሮሚያ /ሰሜን ሸዋ፣ ቡኖ በደሌ/፣ ሶማሌ፣ ደቡብ (ወላይታ፣ አሪ) እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ውስጥ በተካሄዱት የውይይት መድረኮች፣ በሰላም ዕጦት የወደሙ ትምህርት ቤቶች እና ጤናን ጨምሮ የሌሎች ተቋማት መልሶ ግንባታ፣ የውኀ አቅርቦት መቋረጥ፣ የባንክ አገልግሎቶች ዕጥረት እና ሕገ-ወጥ የድንበር ንግድን የመከላከል አስፈላጊነት ላይ ሰፋ ያሉ ውይይቶች ተደርገዋል። የሠላም እና የፀጥታ ጉዳይ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ መንግስት ዘላቂ ሠላም ማስፈን እና የዜጎችን መብት ማስከበር እንዳለበት ተነስቶም ምክክር ተካሄዶበታል።

ከእነዚህ ኹለት አንኳር ጉዳዮች በተጨማሪም፣ የመልካም አሥተዳደር ችግሮች፣ የተፈናቃዮች ወደቀያቸው የመመለሳቸው ኹኔታ፣ የልማት ዕቅዶች አፈፃፀም መጓተት እና የመንገድ ሥራዎች መጓተቶች በመራጮቹ በኩል ተነስተው ውይይቶች ተካሂደውባቸዋል። ከአራት ዐሥርት በላይ በሚሆኑት እነዚያ የተመራጭ-መራጭ ውይይቶች ላይ የተነሱት እነዚኽ ብቻም ሳይሆኑ፣ ከመድኀኒት ዕጥረት እስከ የመብራት እና የስልክ ግንኙነት አገልግሎት መጓደል፤ ከሥራ አጥነት እስከ የኑሮ ውድነት፤ ከማዳበሪያ ዋጋ ንረት እስከ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ውስንነት፤ እንዲኹም የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ጉዳይ እና ከልማት ጋር የተያያዙ የግብር ክፍያዎች መዘግየት በእነዚያ ውይይቶች ተደጋግመው የተነሱ አጀንዳዎች ነበሩ።

## የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት











# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ እንዲፈፀሟቸው ከሚጠበቁባቸው የእንደራሴነት ኀላፊነቶች ሌላይኛው አሥፈጻሚ ተቋማትን መቆጣጠር ነው። በዚኽ ረገድም፣ የአሥፈጻሚ ተቋማትን ሪፖርት ማድመጥ፣ ተቋማቱን በአካል ተገኝቶች መገምገም እና የመስክ ጉብኝቶች ማድረግ የሚጠቀሱት ናቸው።



## የተቋማት ሪፖርቶች

የተለያዩ የፌዴራሉ መንግስት ተቋማት፣ ለሚጠሩባቸው የተለያዩ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከ8 እስከ 9 ወራት የሚሸፍነውን የሥራ አፈፃፀማቸውን ሪፖርት በወርሃ መጋቢትም አቅርበው ነበር።

በቀዳሚነት መጋቢት 15 ቀን በዋለው ምክር ቤት፣ የ2017 ዓ.ም. የስምንት ወራት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቱን ያቀረበው፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የተሰኘው የቅርብ ጊዜው ተቋም ነበር። የተቋሙን ሪፖርት ለምክር ቤቱ የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡት ሥራ አሥፈፃሚው ብሩክ ታዬ፣ የሚመሩት ተቋም በግማሽ ዓመቱ 901 ቢሊዮን ብር ገቢ ማመንጨቱን ተናግረዋል። ሥራ አሥፈፃሚው አክለውም፣ 14 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የመንግስት ትርፍ ድርሻ ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ተደርጓል ብለዋል።[1]

በወሩ የሪፖርት አቀራረብ ቅደም-ተከትል በኹለተኛነት ሪፖርቱን ያቀረበው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነበር። መጋቢት 25 20117 ዓ.ም. የባንኩን የስምንት ወራት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡት የባንኩ ፕሬዝደንት አቤ ሳኖ፣ ባንኩ ባለፉት ስምንት ወራት የ32.6 ቢሊዮን ብር ትርፍ አስመዝግቧል ብለዋል። ለቋሚ ኮሚቴው በቀረበው ሪፖርት፣ ባለፉት ስምንት ወራት ከተሰጠው ጠቅላላ ብር 264.65 ቢሊዮን ብድር ውስጥ፣ ከ88% በላይ ብድር የተሰጠው ለግሉ ዘርፍ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፣ አኹን ያለው የመንግስት ተቋማት የብድር ክምችት ድርሻ ደግሞ ወደ 72% ዝቅ ማለቱ ተመላክቷል። በኹሉም የባንኩ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ላይ አበረታች አፈጻጸም የተመዘገበ መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዝደንቱም፣ ባንኩ አምና በተመሳሳይ ወቅት ካገኘው ገቢ 26 በመቶ ዕድገት በማሳየት 109.32 ቢሊዮን ብር ጠቅላላ ገቢ ማግኘቱን አስታውቀዋል። የባንኩ አጠቃላይ ተቀማጭ ብር 1.54 ትሪሊዮን በላይ መድረሱን ያነሳው የአቤ ሪፖርት፣ በዚህም የባንኩ የገበያ ድርሻ ወደ 49.3% ከፍ ማለቱን አውስቷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መሐመድ አብዶ በበኩላቸው፣ ባንኩ የኢንዱስትሪውን ሰላም ከማስጠበቅ አኳያ እና ለግሉ ዘርፍ 80% ብድር መስጠቱ ንግዱ እንዲሰለጥን ያግዛል ሲሉም ተደምጠዋል።

መጋቢት 24 2017 ዓ.ም. ተረኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም፣ በ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና የተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ የሆነበትን መንስዔ በተመለከተ ከአጋር አካላት ጋር ያስጠናውን ጥናት፣ ለምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል። ጥናቱን ለኮሚቴው ያቀረቡት የትምህርት ፕሮፌሰር ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ፣ ለተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል የተለያዩ ጉዳዮችን በምክንያትነት አንስተዋል። የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በዩኒቨርሲቲ መስጠት መጀመራችን ሆን ተብሎ ሲደበቅ የነበረውን ጉድ

1 የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “የልማት ድርጅቶች የሕዝብ ጥያቄዎችን የዕቅዳቸው አካል ሊያደርጉ እንደሚገባ ተመላከተ።” https://web.facebook.com/share/p/1HM3edL1ND/



የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ሥራ አሥፈፃሚው ዶ.ር. ብሩክ ታዬ ሪፖርቱን በማቅረብ ላይ

ገልጦ ገሃድ አውጥቷል ያሉት ብርሃኑ፣ ለተማሪዎች ውጤት ውድቀት ባለድርሻ አካላት በብልሹ አሰራር ተባባሪ ናቸው ብለዋል። 8ኛ ክፍል ደርሰው ማንበብ የማይችሉ ተማሪዎች ነበሩ ያሉት የትምህርት ሚኒስትሩ፣ ጥናቱ ሊያሳየው የማይችለው የአገራችን የትምህርት ችግር ዋናው መሠረቱ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ላይ የደረሰውን የሞራል ክስረት ነው ብለዋል። ችግሩን ለመፍታት የመምህራንን የኑሮ ኹኔታ ማሻሻል ቁልፍ ጉዳይ ቢሆንም፣ የአገሪቷ ኢኮኖሚ ግን ጉዳዩን መሸከም እንደማይችል የጠቀሱት ብርሃኑ፣ አገሪቷ ከ100 ሺህ በላይ የመምህራን ዕጥረት እንዳጋጠማትም ገልጸዋል።

በወርሃ መጋቢት በአራተኛነት ተቋማዊ ሪፖርቱን ያቀረበው የማዕድን ሚኒስቴር ሲሆን፣ ተቋሙ የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ለእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል። የአፈፃፀም ሪፖርቱን ያቀረቡት ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ፣ ከዚህ ቀደም በማዕድን ዘርፍ ላይ በትልቅነት የተመዘገበው 800 ሚሊዮን ዶላር እንደነበር ጠቅሰው፣ በዚህ ሪፖርታቸው በሸፈናቸው ስምንት ወራት ውስጥ ግን ተቋማቸው 1.88 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማስመዝገቡን ተናግረዋል። ከዚህ የውጭ ምንዛሬ ውስጥም፣ ወርቅ ትልቁን ድርሻ ይዟል ተብሏል።[2]

የወርሃ መጋቢት የመጨረሻው ሪፖርት የነበረው፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የራድዮ እና የቴሌቪዥን፣ የዜና እና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ነበር። በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የራድዮ እና የቴሌቪዥን፣ የዜና እና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ውጤታማነት በተመለከተ፣ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም. ድረስ ያለው የኦዲት ሪፖርት ለምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ቀርቧል። በመድረኩም፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተሯ መሰረት ዳምጤ፣ ተቋሙ ከነበረበት ኹኔታ መሠረታዊ ለውጥ እንደታየበት ተናግረዋል። ዋና ኦዲተሯ፣ በተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያዎች መረጃዎችን ማስተላለፉ በጥሩ ጎን የሚታይ መሆኑንም አክለው ጠቅሰዋል። የኢቢሲ ዋና ሥራ አሥፈፃሚው ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፣ በለውጡ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ኅብረተሰቡ በተለያየ መልኩ ሐሳቡን የሚሰጥበት ኹኔታ የተመቻቸ መሆኑን እና ተቋሙንም የሐሳብ ተቋም ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።[3]

2 የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “ቋሚ ኮሚቴው፣ ከአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ አንዱ የሆነው የማዕድን ዘርፍ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በትኩረት መስራት እንደሚገባ አሳሰበ።” https://web.facebook.com/share/p/12J3Ghbp2p1/

3 ኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “‘ሚዲያው ተወዳዳሪ፣ ተደማጭና ተአማኒነት ያለው የመረጃ ምንጭ ለመሆን የጀመራቸው ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው’ ቋሚ ኮሚቴው።” https://web.facebook.com/share/p/1FSvBHVEkW/

## የተቋማት እና የመስክ ጉብኙቶች

ኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮቹ ምክር ቤት፣ 32 የሚሆኑ የመስክ ጉብኝቶችን ጨምሮ፣ የተለያዩ የፌዴራል እና ክልላዊ ተቋማትን አኹናዊ ኹኔታም በተወካዮቹ በኩል ጎብኝቷል።

### የተቋማት ጉብኙቶች

በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙት ተቋማት ውስጥ ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉት መካከል፣ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ይገኝበታል። መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት በማተሚያ ቤቱ በተደረገው ጉብኝት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎችን ወደ ዘርፉ በማስገባት ተቋሙን ተወዳዳሪ ማድረግ መቻሉ ተነግሯል። የማተሚያ ቤቱ ዋና ሥራ አሥፈጻሚ ሽታሁን ዋለ፣ የኅትመት ዘርፉ ተለዋዋጭ ቴክኖሎጂ ያለበት መሆኑን ለኮሚቴው አባላት ጠቁመው፣ ድርጅቱ የሚጠቀምባቸው አብዛኛዎቹ የኅትመት መሣሪያዎች ግን ከዘመኑ ጋር እንደማይሄዱ አብራርተዋል። የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም፣ በተጠቀሰው ወር በእንደራሴዎቹ የተጎበኘ ሌላኛው የፌዴራል መንግስቱ ተቋም ነበር። መጋቢት አጋማሽ ላይ፣ በእንደራሴዎቹ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ነገሪ ሌንጮ በተመራው ይኸው የኮሚሽኑ ጉብኝት፣ የተቋሙ የማሻሻያ ሥራዎች ምን ላይ እንደደረሱ ኮሚቴው ገምግሟል። የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ መኩሪያ ኃይሌ፣ ሲቪል ሰርቪሱ ኢትዮጵያን በሚመጥን ደረጃ እንዲሆን በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ጠቅሰው፣ በዚኽም የተደራጀ መረጃ አያያዝን የተከተለ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት አብራርተውላቸዋል። ቋሚ ኮሚቴውም፣ የተቋሙን የቢሮ አደረጃጀት፣ የተለያዩ አገራዊ ስያሜ ያላቸውን ዘመናዊ የአሥተዳደር ፍርድ ቤት የችሎት እና የሥልጠና አዳራሾችን ጨምሮ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ አኹናዊ ኹኔታን ተመልክቷል።

የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክም፣ በወርሃ መጋቢት ከተጎበኙት ተቋማት መካከል የሚጠቀሰው ነው። በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት በተካሄደው ይኸው ጉብኝት፣ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ከገጠመው ፈታኝ ኹኔታ በማገገም ዐሥር ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን እና ለውጭ ገበያ በሚያቀርባቸው ምርቶችም ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ መሆኑ ተነስቷል። ይኸም ሆኖ፣ ከሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር የሚነሱት ጥያቄዎች መፍትሔ ሊያገኙ እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል። የፓርኩ ዋና ሥራ አሥኪያጅ አሕመድ ሰኢድ በበኩላቸው፣ የኢንዱስትሪ ፓርኩ ከተከፈተ ጊዜ አንስቶ በርካታ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ መግባታቸውን እና በዚኽ የተነሳም ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ሰባት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል።[1]

### የመስክ ጉብኙቶች

በወርሃ መጋቢት፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ወደ መስክም ወርደው ሰፋ ያሉ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ጉብኝቶች አድርገዋል። መጋቢት መገባደጃ ላይ ወደ ሐረሪ ክልል ጎራ ያሉት የምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በክልሉ በሚያ ወረዳ የሚገኘውን የንጹሕ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክትን ጎብኝተዋል። ኮሚቴውን የመሩት እንደራሴው ወልደየስ ደበበ፣ በከተማዋም ሆነ በዙሪያዋ እያጋጠመ ያለው የንጹሕ መጠጥ ውኃ ዕጥረት በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲያገኝ አሳስበዋል።። ከዚኽ በተጨማሪም ኮሚቴው፣ የፕሮጀክቱ የግንባታ ሥራ ዘጠና ስምንት በመቶ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ባለመጀመሩ ስጋት እንዳለው ለክልሉ ተወካዮች አንስቶላቸዋል። ከዚኽ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት በተጨማሪም፣ በተለይም የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታ ፕሮጀክቱ የሥራ ክንውን ገና ስድስት በመቶ ላይ የሚገኝ መሆኑን የጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴው፣ ፕሮጀክቱ ከተያዘለት ጊዜ በእጅጉ መዘግየቱ እንዳሳሰበው ለከተማይቱ

---

1 የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ እያሳየ ያለው ዕድገት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተመላከተ” https://web.facebook.com/share/p/1NPvnJEEJ2/


ጉብኝት በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት


ጉብኝት በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ



ጉብኝት በሎሜ እና ቦራ ወረዳ

ተወካዮች ጠቅሶላቸዋል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ሎሚ በዶ እና ከምሥራቅ ሸዋ የተወከሉ እንደራሴዎች በሎሜ እና ቦራ ወረዳ ተገኝተው ያደረጉት የመስክ ጉብኝት ደግሞ ሌላኛው የምክር ቤቱ የመጋቢት ወር ክንውን ነበር። ምክትል አፈ-ጉባኤዋ እና እንደራሴዎቹም፣ የተሠሩትን እና በመሠራት ላይ የሚገኙትን የበጋ ስንዴ እና የሙዝ ክላስተር የግብርና የልማት እንቅስቃሴዎችን ብቻም ሳይሆን፣ አዲሱን የገጠር ቀበሌዎች አደረጃጀት ጽሕፈት ቤቶችን እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል። በተጠቀሰው መጋቢት ወር የመጎብኘት ዕድል ካገኙት ፕሮጀክቶች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው፣ የኮይሻ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ጉብኝቱ የተመራውም፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር በሆኑት ተስፋዬ በልጅጌ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ነበር። የኮይሻ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ሥድሳ አምስት በመቶ መድረሱም በጉብኝቱ ወቅት ተነስቷል። >በ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዩሮ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው ይኸ ፕሮጀክት፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኮንታ ዞን ኮንታ ኮይሻ ወረዳ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን መሎ ኮዛ ወረዳ መካከል ላይ እንደመገኘቱ፣ ልማቱ የኹለቱን ክልሎች ሕዝቦች ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በሚፈታ መልኩ እየተገነባ እንደሚገኝም ከመስክ ጉብኝቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ በመጋቢቱ የመስክ ጉብኝቶቻቸው፣ የልማት ዕቅዶችን የት መድረስን ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጠሮ አደጋ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎች አኹን ያሉበትን ኹኔታም አደጋዎቹ በደረሱባቸው አካባቢዎች ተገኝተው ተመልክተዋል። በእንደራሴዋ ፋንታዬ ለገሰ የተመራው የምክር ቤቱ የውጪ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ቡድን፣ የተፈጥሮ አደጋው ያስከተለውን ውድመት እና ውድመቱ ያመጣውን ዳፋ ለመመለስ የተሠሩ ሥራዎችን አስመልክቶ፣ የከፋ ዞን አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ያቀረበለትን ሪፖርት አድምጧል። ከሪፖርቱ ማድመጥ እና ከመስክ ምልከታው በኋላም ፣ በተፈጥሮ አደጋ ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች መሠረተ ልማት ማሟላት እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አስገንዝቧል። ከዚኽ በተጨማሪም ኮሚሽኑ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከፋ ዞን በመሬት መንሸራተት የተነሳ ሐምሌ 2016 ዓ.ም. እና ጥቅምት 2017 ዓ.ም. በዴቻ እና አድዮ ወረዳ የደረሰውን አደጋም እንዲኹ ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርቷል። በዚያ የመስክ ጉብኝት ወቅትም፣በአደጋው ሳቢያ ከቀያቸው የተፈናቀሉት ዜጎች፣ የፌዴራል መንግስቱ በቀጣይ በቋሚነት የምንሰፍርበት ቦታ አዘጋጅቶ መልሶ ያቋቁመን ሲሉ ጠይቀዋል።



የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ከኩባው አምባሳደር መይሊን ሱዋሬዝ አልቫሬዝ ጋር

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የኢፌዴሪ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በተጠቀሰው መጋቢት ወር ኹለት የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውኖችን ከውኗል። በወሩ መጀመሪያ ላይ፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ በአምባሳደር መይሊን ሱዋሬዝ አልቫሬዝ ከተመራ ልዑክ ቡድን ጋራ ተወያይተዋል። በአፈ-ጉባኤው ቢሮ በተካሄደ ይኸው ውይይት ላይም፣ የኢትዮጵያ እና ኩባ ጠንካራ የወዳጅነት ግንኙነት ሃምሳ ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን ታገሰ ጠቅሰዋል። ከትምህርት እስከ ጤና እና ወታደራዊ ድጋፍ ድረስ፣ ኩባ ለኢትዮጵያ ላበረከተችው አስተዋጽኦ አፈ-ጉባኤው ምስጋናቸውን ለልዑክ ቡድኑ አቅርበዋል:: ታደስ አክለውም፣ ይኸንን ነባር ታሪካዊ የአገራቱን ወዳጅያዊ ግንኙነት፣ በፓርላማ ዲፕሎማሲ እና በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በኩል አጠናክሮ ለማስቀጠል ኢትዮጵያ ጽኑ ፍላጎት አላት ብለዋል፤ የኩባ ባለሃብቶች በመረጡት ዘርፍ በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል:: ልዑክ ቡድኑን የመሩት በኢትዮጵያ የኩባ አምባሳደር መይሊን ሱዋሬዝ አልቫሬዝ በበኩላቸው፣ የኹለቱ አገራት ግንኙነት ጠንካራ እና ታሪካዊ መሆኑን አንስተው፣ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የእህትማማች ትስስሮሽ በሁሉም ዘርፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል ተናግረዋል::

ምክር ቤቱ፣ መጋቢት መጋባደጃ ላይ ያካሄደው ኹለተኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ ኹለቱንም ምክር ቤቶች ያቀፈውን ልዑክ ወደ ኤዢያ በመላክ የተሳተፈበት አንድ ዓለም ዓቀፍ መድረክ ነበር። በፌዴሬሽን ምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር የተመራው ከእንደራሴዎቹ እና ከፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት የተወጣጣው የልዑካን ቡድን፣ በኡዝቤኪስታን በተካሄደው በ150ኛው ዓለም ዓቀፉ የፓርላማ ኅብረት ጉባኤ ላይ ተሳትፏል። በጉባኤው ላይ ተሳተፉት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ ወሳኝ በሆኑ ዓለም ዓቀፋዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የኢትዮጵያን ልምድ እና ተሞክሮ ለዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ማስተዋወቅ የሚያስችለውን ዕድል በአግባቡ መጠቀማቸውን ገልፀዋል።

በዚኹ መድረክ ላይ የተሳተፉት በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ምረቱ ሻንቆ፣ "የነገዎቹን ሉላዊ መሪዎችን ማጎልመስት" በሚል ርዕስ መልዕክት አስተላልፈዋል። ሚኒስትር ዴኤታው በዚያ ንግግራቸው፣ ወጣቶችን ያላማከለ የፖለቲካም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ቀጣይነት እንደማይኖረው ገልፀው፣ በተጨባጭ የወጣቶችን ተሳትፎ እና ሚና ማሳደግ እንደሚገባ አውስተዋል። የመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች፣ ሰላም ግንባታ፣ ዘላቂ ልማት እና ፍትሓዊ ተጠቃሚነት እና የአየር ንብረት ለውጥን የመሳሰሉት አጀንዳዎች የኅብረቱ የመወያያ አጀንዳዎች ነበሩ።

# የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የፌዴራል መንግሥቱ በክልሎቹ ውስጥ ጣልቃ የሚገባበትን ነባር አዋጅ አሻሽሏል። ምክር ቤቱ፣ መጋቢት 23 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 22ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የቀረበለትን ይኸንኑ የማሻሻያ አዋጅ ያፀደቀው በኹለት ድምጸ-ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ ሲሆን፤ ነባሩን አዋጅ ቁጥር 359/1995ን ተክቶ አዋጅ ቁጥር 1373/2017 በሚል አፅድቆታል።

## በአዋጅ ቁጥር 1373/2017 ላይ የተደረገ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ

ይኸ የተሻሻለው አዋጅ (ቁጥር 1373)፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን እና የፌዴራል መንግሥቱን ተቋማዊ አቅም በመገንባት ረገድ፣ በተለይም የፌዴራል መንግሥቱ በትግራይ ክልል ጣልቃ የመግባቱ የመጀመሪያው ዙር በተገባደደ ማግስት ያጋጠሙ አሠተዳደራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት የሕግ እና ፖለቲካዊ ክፍተቶችን ለመድፈን ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል። በሌላ በኩል በትግራይ ክልል ካጋጠመው ኹኔታ በመነሳት፣ በሌሎች የፌዴሬሽኑ አባላት ውስጥ መሰል ችግሮች ቢከሰቱ፣ ታጣቂ የፖለቲካ ቡድኖች የበላይነትን፣ የጊዜያዊ አሠተዳደሩ በልማት እና የአሠተዳደር ዘርፍ በሚጫወተው ሚና ዙሪያ ላይ እና ተያያዥ ጉዳዮች እንዴት እንደሚፈቱ አኹንም በግልፅ አለመቀመጡን ብሪጅ ተረድቷል።

በመሆኑም ይኸ አጠር ያለ ኀተታ የቀዳሚውን አዋጅ ውስንነቶች፣ በትግራይ ክልል ስላጋጠመው የሕግ እና የፖለቲካ ነባራዊ ክፍተቶች እንዲኹም የተሻሻሉ ጉዳዮችን እና አንድምታዎችን ይፈትሻል።

## የአዋጅ 359/1995 ውስንነቶች

በ1987ቱ ሕገ-መንግሥት በዝርዝር እንደተቀመጠው፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀር፣ የብሔር፣ ብሔረ ሰቦች እና ሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መርህ ላይ የተመሠረተ ነው። የሕዝቦች ባህላዊ ማንነት እና ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣ ከፍተኛ ልዕልና የተሰጣቸው የሕገ-መንግሥቱ ቀዳሚ አዕማድ ናቸው። አኹን እንዲሻሻል የተፈለገው ነባሩ አዋጅ 359 አስፈላጊ የሆነበት ምክንያትም፣ በመሠረታዊነት ይኸን በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገውን የሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ቡድናዊ መብት የመጣስ አደጋ ሲገጠመው እና በተራዛሚውም ሕገ-መንግሥቱን የሚያናጉ ፖለቲካዊ ኹነቶች ሲፈጠሩ መሆኑ ግልፅ ነው። የነባሩ አዋጅ ጥቅል መነሾም፣ የፌዴሬሽኑ አባላት ወደ ሕገ-መንግሥታዊው ሥርዓት እንዲመለሱ እና ሥርዓቱንም ሊመጣበት ከሚችልበት የመናጋት ተጨባጭ አደጋ ለመካለከል ነበር። የተፈጠረውን ችግር ቀልብሶ፣ ፖለቲካዊ ሥርዓቱን ወደነበረበት ሕገ-መንግሥታዊ ድባብ ለመመለስም፣ በአዋጁ እንደተቀመጠው ጊዜያዊ አሠተዳደርን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ አሌ አይባልም።



ነገር ግን አዋጁ የጊዜያዊ አሠተዳደር ቆይታን በኹለት ዓመታት ብቻ ከመገደቡ ባለፈ፣ ለጊዜያዊ አሠተዳደሩ መቋቋም መነሾ የሆኑት ኹሉም ነባራዊ ችግሮች በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ይፈታሉ ብሎ ማመኑ የሚከተሉትን ውስንነቶች አዋልዷል።

የአዋጁ አንቀጽ 15 ቁጥር 3፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተጠቀሰው ክልል ችግር አልተፈታም ብሎ ካመነ፣ የመቆያ ጊዜውን ከሥድስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የማራዘም ሥልጣን ሰጥቶታል።ይኸ ደግሞ፣ በትግራይ ክልል እንደታየው፣ ነባራዊ ኹኔታን ያገናዘበ አልነበረም።

ሕገ-መንግሥታዊ እክል በተፈጠረበት ክልል ውስጥ የሚቋቋመውን ጊዜያዊ አሠተዳደር ቆይታን ለማራዘም ውሳኔ እንዲሰጥ ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዓመት ኹለት ጊዜ ብቻ የሚሰበሰብ መሆኑ፣ በእነዚኽ የስብሰባ ቀነ-ቀጠሮ ክፍተቶች መካከል፣ አዋጁ እንዲፈታቸው የሚጠበቅበት ችግሮች እየተባባሱ ከመሄዳቸው ባሻገር፣ ከቁጥጥር ውጪ ሊወጡ የሚችሉበትን ዕድል ያሰፋል። ይኸም ሰፊ ሕገ-መንግሥታዊ የአተገባበር ክፍተቶችን ወደመፍጠር ሊያሻግራቸው ይችላል።

እነዚህ እና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች፣ ከኹለት ወራት በፊት የአሠተዳደር ዘመኑ በተጠናቀቀው የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አሠተዳደር ክንውን ላይ እስከታዩበት ጊዜ ድረስ፣ በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ ብቻ የነበሩ ቢሆንም በተጨባጭ መከሰት መቻላቸው አዋጁን ማሻሻልን አስገዳጅ አድርጌታል።

## ትግራይ እንደ ማሳያ

የፌዴራል መንግሥቱ ሕወሓትን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ ጦርነት ቀስቅሷል በሚል በመወንጀል፣ ሕወሓት መራሹን ክልላዊ መንግስት አስወግዶ ጊዜያዊ አሥተዳደር ካቋቋመበት ጊዜ አንስቶ፣ በርካታ ሕግ-ነክ ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይተዋል። ጊዜያዊ አሥተዳደሩ፣ ምርጫ እንደማድረግ ያሉ የተቋቋመባቸውን ግቦች ሳይፈፅም የቆይታ ጊዜውን ካገባደደ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እስኪሰበሰብ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚችለው ሕገ-መንግሥታዊ አካል ማን ነው? የአሥተዳደሩ መቋቋምን አስፈላጊ ያደርጉት ችግሮች እየተባባሱ ቢሄዱስ ፈጣን እርምጃዎች ለመውሰድ ምን ዓይነት ሕገ-መንግሥታዊ መሠረቶች አሉ? በትግራይ ያሉት የፖለቲካ ኃይሎች ግጭት ውስጥ ባሉበት ኹኔታ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንዴት መመለስ ይቻላል? የተፈቀደው የአሥተዳደሩ ዘመነ-ሥልጣን ተገባዶም ክልሉ ከቀውስ መውጣት ባይችል ምን ዓይነት ሕጋዊ እና አሥተዳደራዊ መውጫ መንገዶች አሉ? የሚሉት ተጠቃሾቹ ጥያቄዎች ነበሩ።

> *የአዋጁ አንቀጽ 15 ቁጥር 3፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተጠቀሰው ክልል ችግር አልተፈታም ብሎ ካመነ፣ የመቆያ ጊዜውን ከሥድስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የማራዘም ሥልጣን ሰጥቶታል።ይኽ ደግሞ፣ በትግራይ ክልል እንደታየው፣ ነባራዊ ኹኔታን ያገናዘበ አልነበረም።*

እነዚህ እና ሌሎች በዝርዝር ሊኬድባቸው የሚቻልባቸው ተያያዥ ችግሮች በተጨባጭ መታየታቸው፣ ለነዚኽ ችግሮች ሊሰጡ የሚችሉት ሕጋዊ ምላሾች ከነባሩ አዋጅ ማዕቀፍ የሚያስወጡ እንደመሆናቸው፣ የፌዴራል መንግሥቱን አፋጣኝ ዕርምጃዎችን እንዲወስድ ማስገደዳቸው ግልፅ ነው።ከዚኽ አኳያ ነገሮቹን ስናጤናቸውም፣ በነባሩ አዋጅ መንፈስ እና በተጨባጭ ፖለቲካው መካከል ያሉትን ክፍተቶች አጉልቶ አሳይቷል።

በመሆኑም፣ አዋጅ 1373/2017 ችግርን ለመቅረፍ አስቀድሞ የተወሰዱ እርምጃዎች ያልፈቷቸውን ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ችግሮች ግንዛቤ ውስጥ ከትቶ የተቀረፀ ማሻሻያ ሕግ ነው።እንዲኽ ዓይነት የሕግ አወጣጥ ሂደቶች አልፎ አልፎ የሚደረጉ እና የችግሮችን መባባስ ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆንም፣ የሕግን ተገማችነት እና ሕገ-መንግሥታዊ ሂደትንን እንዳይሸረሽረው መጠንቀቅ እንደሚያሻ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ሕጎች በሚወጡበት ጊዜ መጪውን ጊዜ ግምት ውስጥ የሚከቱ እና እንደ ተጨባጭ ኹኔታዎች መሻሻል የሚያስፈልጋቸው ከመሆኑም በላይ፣ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት በሕገ-መንግሥቱ የተሰጧቸውን ሥልጣኖች በአግባቡ እንዲወጡ የሚያበረታታ መሆን ይኖርበታል።

## የማሻሻያው ይዘቶች

ለፌዴሬሽን ምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ተጨማሪ ሥልጣን ስለመስጠት፤

የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ በዓመት ኹለት ጊዜ ብቻ የሚሰበሰብ እንደመሆኑ፣ በየትኞቹም ክልሎች ውስጥ የማዕከላዊ መንግሥቱን ጣልቃ-ገብነት የሚያስገድዱ ኹኔታዎች ሲፈጠሩ፣የፌደሬሽን ምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ እንዲገባ ለማዘዝ የሚያስችል ሥልጣን ተሰጥቶቷል። ይህም በአዋጅ 359 የነበረውን ውስኑነት ከመቅረፉ ባለፈ፣ የፌዴራል ተቋማቱ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችሎታቸውን ያዳብራልናጉልህ የሆነ የአዋጁ ማሻሻያ ነው።

ከዚኽ አንፃርም፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ የአፈ-ጉባኤውን ውሳኔ መርምረው ውሳኔ የሚያሳልፉ እንደመሆናቸው፣ የማሻሻያው መንፈስ በፌዴሬሽን ምክር ቤቱ የተወከሉትን የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሕገ-መንግስታዊ በጋራ የመወሰን ሥልጣንን ያስጠብቃል፤ ያጠብቃልም።

## ለጊዜያዊ አሥተዳደሮች የሚሰጥ የጊዜ ገደብ

ነባሩ አዋጅ፣ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከሚመጣ አደጋ እንዲከላከሉ የሚቋቋሙ ጊዜያዊ አሥተዳደሮች የተመደበላቸው ጊዜ ሲያበቃ፣ ከሥድስት ወራት በላይ ማራዘም እንደማይቻል ደንግጎ ነበር። ያም ሆኖ፣ መጠነ ሰፊ ደም አፋሳሽ ግጭቶች እና ውስብስብ የፖለቲካ ኹኔታዎች ለሚገጥሟቸውጊዜያዊ አሥተዳደሮች ተጨማሪዎቹ ሥድስት ወራት በቂ አለመሆናቸውን በትግራይ ክልል ከነበረው ኹኔታ በተጨባጭ መረዳት ተችሏል። ይህን ግንዛቤ ውስጥ በመክተትም አዋጅ 1373/2017፣ የአሥተዳደሮቹን ጊዜ እስከ አንድ ዓመት ማራዘም እንደሚቻል እና አስፈላጊ ከሆነም በድጋሚ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም እንደሚችል ደንግጓል።

## የማሻሻያው ጠንካራ እና ደካማ ጉኖች

### ጠንካራ ጎኖች

- በፌዴሬሽን ምክር ቤት ስብሰባ መዘግየት ምክንያት፣ የማዕከላዊ መንግሥቱን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችን የማስከበር ኃላፊነት እንዲወጣ ለማድረግ አፋጣኝ ሕጋዊ መደላደልን መፍጠሩ፤
- የሚቋቋመው ጊዜያዊ አሥተዳደር የተፈጠሩትን ሕጋዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች መፍታት የማይችልባቸው ገደቦች ሲያጋጥሙት፣ የቀሩትን ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራት እንዲፈፅም አስፈላጊ ሲሆን ከሥድስት ወራት በላይ

እንዲኖረው መፈቀዱ፤

- የጊዜያዊ አሥተዳደሩን ቆይታ ማራዘም ሲያስፈልግ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ካለባቸው ተደራራቢ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት አኳያ ምክር ቤቱን በአጭር ጊዜ ስብሰባ በመጥራት ውይይት አድርጎ ውሳኔ ለመሥጠት የሚያስቸግር ኹኔታን ግንዛቤ ውስጥ መክተቱ፤

- የሚቋቋመውን ጊዜያዊ አሥተዳደር በተመለከተ፣ በአፈ-ጉባኤው በሚሰጥ አልያም በምክር ቤቱ በሚጸድቅ ውሳኔ ውስጥ ጊዜያዊ አሥተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የሚመላከቱበት ኹኔታ እንዳለ በማሻሻያው መካተቱ፤

- የሕጎች መሻሻል አንዱ ገፊ ምክንያት፣ ከነባራዊ ኹኔታዎች ጋር መናበብ መቻላቸው ከመሆኑ አኳያ፣ ማሻሻያው ለትግራይ ክልል አኹናዊነት ምላሽ ሊሰጥ መቻሉ፣ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉት ናቸው።

## ደካማ ጎኖች

- ምንም እንኳን ማሻሻያው የፌዴሬሽን ምክር ቤቱን በአጣዳፊ ሰብስቦ ውሳኔ መስጠት አለመቻልን ተንተርሶ፣ የጊዜያዊ አሥተዳደሩን ርዝማኔ ጉዳይ ለአፈ-ጉባኤው መስጠቱ በጎ ጎኑ ቢሆኑም ቅሉ፣ የአፈ-ጉባኤውን ውሳኔ ምክር ቤቱ እንዲያፀድቅ መደንገጉ፣ በአፈ-ጉባኤው ውሳኔ እና በፌዴሬሽን ም/ቤት አባላት የመሰብሰቢያ ጊዜ መሀል ያለው ክፍተት ተጠያቂነትን የሚያላላ እንዳይሆን ያሰጋል፤

- የጊዜያዊ አሥተዳዳሮች የአሥተዳደር ጊዜ በተራዘመ ቁጥር፣ በሕዝቦች የቋንቋ ማንነት ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀር በተለይም የክልል ራስ ገዝ አስተዳደርን የማዳከም ስሜት ሊፈጥር ይችላል። ሕጋዊ ትክክለኝነት ቢኖረውም፣ የፖለቲካ ስሜቶችን እንዳያከራቸውም ያሰጋል።

## አንድምታዎች

ከላይ በአጭሩ የዳሰስነው ይኽ የተሻሻለው አዋጅ 1373/2017፣ የነባሩን አዋጅ 359ን ውስንነቶች በቀረፈ መልኩ ከፀደቀበት መጋቢት 23 ጀምሮ ወደሥራ ገብቷል። አዋጁም፣ ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ቀውሶች ሲገጥሟት በሆነ ልክ ችግር መፍቻ ዘዴ ሆኖም እንደሚቀጥል ይታመናል። አዋጁ በተቀመጠለት የማሻሻያ መንፈስ ከተተገበረ፣ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በቅጡ ለማስከበርም ይረዳል የሚል ዕምነት አለ። ይኽ ካልሆነ ግን፣ አሳታፊነትን እና የብዝሓ ብሔርነትን ቅርጽ ይዞ የተነሳውን ሕገ-መንግሥት እንዳይሸርሸር ያሰጋል። እንደማንኛቹም ሕግጋት፣ ይኽም ማሻሻያ እንዲደረግለት የተገደደው ሕግም ብቻውን ለሚፈተሩ ፖለቲካዊ ቀውሶች መፍትሔ እንደማያመጣ ግልጽ ነው፤ የሕጉ ትግበራ የታለመለትን መፍትሔ እንዲያመጣ ከተፈለገ፣ ከሕጉ ጋር ተናባቢ የሆኑ ተቋማዊ ለውጦችን ማምጣት አስፈላጊ ነው። በተለይም ተጨማሪ የጊዜያዊ አሥተዳደሩን ማራዘሚያዎች ማስቀረት የሚቻለው፣ ያ እንዳይከሰት የሚያረጋግጡ አንዳንድ ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ እርምጃዎችን መውሰድ ሲቻል ብቻ ነው። ከዚኽ አኳያም፣ የሚቋቋመውን ጊዜያዊ አሥተዳደር የሥልጣን ዘመን ማራዘም መቻሉ ብቻ፣ ሥራ አሥፈፃሚውን በአስቸኳይ መንፈስ ሥራዎቹን እንዳይሠራ እንዳያዘናጋው አንዳች መላ ማበጀትም አስፈላጊ ይሆናል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የክትትል እና የቁጥጥር መላዎችን መንደፍና መተግበር፣ እንዲኹም የጊዜያዊ አሥተዳደሮችን የአፈፃፀም መመዘኛዎች በግልጽ ማስቀመጥ፣ አዋጁ የተቀመጠለትን ግብ ለማሳካት ዓይነተኛ አበርክቶ እንደሚኖራቸው ማስታወስ እንሻለን።

## መደምደሚያ

የአዋጅ 1373/2017 መጽደቅ አገራዊ አንድነትን እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን ለማጽናት እንዲኹም ብዝሓነትን እና ያልተማከለ አሥተዳደርን ለማረጋገጥ ነባራዊ ሕጎችን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ አሳይቷል። አዋጁ የቀደሙ ክፍተቶችን ለመሸፈን ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም፣ ውጤታማነቱ የሚረጋገጠው ግን እንደ ማኅበረሰብ በምናራምደው የፖለቲካ አቋም ብቻ ነው። የሕገ-መንግሥቱ መሠረታዊ ዕሴቶች የሆኑት ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እና በጋራ የመወሰን ሥልጣን እንዳይሸረሸሩና የጊዜያዊ አሥተዳደሮቹን እንዲኹም የማዕከላዊ መንግሥቱን ጣልቃ-ገብነቶች በጊዜያዊነቶች ላይ ብቻ እንዲገደቡ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ይኽ እንዲሳካ ደግሞ፣ ሥልጣን እና ተጠያቂነትን የማይነጣጠሉ ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች ማድረግ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን፤ ስለምን ቢሉ፣ ጠንካራ እና በዴሞክራሲያዊ ኅብረ-ብሔራዊ መርህ ላይ የተመሠረተ ፌዴራሊዝም የሚተገበረው በዚህ መንገድ ብቻ ነውና!

## የመስክ ስራዎችን በተመለከተ ዳሰሳዊ ምልከታ

ኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ወደ‘ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ፣ ከወከሏቸው መራጮቻቸው እና በየአካባቢዎቻቸው ከሚገኙ ተቋማት ጋር በቀጥታ በመገናኘት የመስክ ጉብኝቶችን አድርገዋል። በዚኽ የመስክ ጉብኝቶቻቸውም፣ በሄዱባቸው አካባቢዎች ስለተከናወኑና በመከናወን ላይ ያሉ የልማት እንቅስቃሴዎችን እና ተግዳሮቶችን በመገምገም ተጨባጭ መረጃ ማግኘት ችለዋል። በዚኽም፣ ሕገመንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ባሻገር የመንግሥትን እና የኅብረተሰቡን ግንኙነት ወደ ተሻለ ከፍታ ያስቻሉ ኹነቶችን ፈጥረዋል።

ለማሳያ ያህልም፣ እንደራሴዎች በመጋቢት ወር ውስጥ ካደረጓቸው የመስክ ጉብኝቶች መካከል፣ የኮይሻ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብን እና የኮምቦልቻን ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ላይ ያደረጉት ጉብኝት ተጠቃሽ ነው። እንደራሴዎቹ በዚኽ የመስክ ምልከታቸው ያካተቱት፣ ከግብርና እስከ መሠረተ-ልማት እና አደጋ መከላከል፤ እንዲኹም የመንግሥት አገልግሎትን እስከ ማሻሻል ያሉትን የጨመረ ነበር። የመስክ ምልከታዎቻቸው በቅርብ ከሚያገኙት አዲስ አበባ ጀምሮ፣ ራቅ ያሉትን እስከ ከፋና ጋሞ ዞኖችን ያካተቱ እንደመሆናቸው፣ ይኽን መሰሎቹ የቋሚ ምልከታዎች፣ እንደራሴዎቹን ሙሉ ስዕል እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

በዚኽ የመጀመሪያ ዕትማችን የሚኖረን የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፣ እንደራሴዎቹኮምቦልቻ የኢንዱስትሪ ፓርክ ጉብኝትን በዓበይትነት ያነሳል። ምንም እንኳን፣ እንደራሴዎቹ የውክልና ሥራዎቻቸውን በዚኽ መልኩ እየተወጡ ቢሆንም፣ በመስክ ምልከታቸው ወቅት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የመፍትሔ አካል ለመሆን የክትትል ሥርዓት መከተል ያስፈልጋቸዋል፤ ይኽ የክትትል ሥርዓት እስከ አኹን ካለም ለሕዝብ ግልጽ መሆን ይኖርበታል ብለን እናምናለን፤ ከዚኽ በተጨማሪም፣ የእንደራሴዎቹ ምልከታ ያስከተላቸው ለውጦች መኖር አለመኖራቸው በተለይም የመስክ ምልከታው ለተደረገባቸው ተቋማት ኹነኛ ሚና ይኖረዋልና፣ ይፋ መደረግ እንዳለበት ብሪጅ ያምናል። በዚኽ ጉዳይ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ለምሳሌ የኬንያ እንደራሴዎች ከሕዝብ ጋር ከሚያገናኟችው መድረኮች በተጨማሪ፣ በየምርጫ ክልሎቻቸው ቢሮዎች ብቻም ሳይሆን፣ ቅሬታዎችን የሚቀበሉና የሚመለከቷቸውን የልማት ፕሮጀክቶችን የሚከታተሉ ሠራተኞች ጭምር አሏቸው።[1] ከዚኽ መገናኛ አማራጭ በተጨማሪም፣ የዲጂታል እና የማኅበራዊ ሚድያን በመጠቀም ከመራጮቻቸው ጋር ይወያያሉ። ከዚኽ ባለፈም አንዳንድ የአገሪቷ እንደራሴዎች፣ በየአካባቢዎቻቸው ስላሉ ማኅበረ-ፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች አልያም በሂደት ላይ ባሉ ፕሮጀክቶች ማኅበረሰባዊ ቅቡልና ዙሪያ የተዋቀረ ግብረ መልስ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ የመነሻ ጥናቶችን ያካሂዳሉ።

ወደ እኛ አገር መልስ በማለትም፣ ለማሳያነት ባነሳነው የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የእንደራሴዎቹ ጉብኝት ዙሪያ ጥቂት ምክረ-ሐሳቦችን መሰንዘር እንሻለን። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉብኝታቸው ወቅት የተመለከቷቸውን እንደዝቅተኛ ደመወዝ እና ያልተሟላ የኑሮ ኹኔታ ዙሪያ ለፓርኩ የሥራ ኃላፊዎች ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።ከዚኽ አንፃርም፣ እንደ ብሪጅ ዕይታ፣ የቋሚ ኮሚቴው አባላት ይኽን መሰሉን ማሳሰቢያ ከመስጠት ባሻገር፣ ማሳሰቢያቸው መፈፀሙን/አለመፈፀሙን የሚከታተሉበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ክትትል ማድረግ ይገባቸዋል። ከአራት ዓመታት በፊት የተሰራው የዓለም ባንክ ጥናት[2] እንደሚያሳየው፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ የሚከፈለው ክፍያ፣ ከአካባቢው የመሠረታዊ ፍላጎቶች ወጪ ጋር ሲነፃፀር በሌሎች የአገር ውስጥ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከሚከፈለው ክፍያ ጋር ተመሳሳይ ነበር። ምንም እንኳን ሌሎች ጥናቶች፣ በክፍያ ዙሪያ አከራካሪ መረጃዎችን ቢያመለክቱም፣ የባንኩ ጥናት የሠራተኞች አማካኝ ጥቅል ክፍያ፣ በአካባቢያዊ ካለው የድኅነት ወለል አንፃር ሲለካ ከሚገኘው የክፍያ ምጣኔ አኳያ ወደ አራት ዕጥፍ ገደማ ከፍ የሚል እንደነበር ያሳያል። ነገር ግን ይኸው ጥናት፣ የማካካሻ እና

---

1 Parliament of Kenya. “Members Services and Facilities Committee collect views from constituency offices' staff”http://parliament.go.ke/members-services-and-facilities-committee-collect-views-constituency-offices-staff

2 World Bank Group. 2021. Wages and compensation in Ethiopia's industrial parks: evidence from a firm survey. https://documents1.worldbank.org/curated/en/834531617685578320/pdf/Wages-and-Compensation-in-Ethiopia-s-Industrial-Parks-Evidence-from-a-Firm-Survey.pdf

የክፍያ መዋቅር በኢንዱስትሪዎች መካከል በእጅጉ መለያየት እና በቂ የሆነ መረጃ አለመኖርን እንደችግር አንስቷል። በተለይ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከተፈጠረው የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም እና የምግብ ዋጋ ንረት ጋር ተያይዞ፣ የኢንዱስትሪው ፓርክ ሠራተኞች በምን ልክ ኑሯቸው እንደታወከ የቋሚ ኮሚቴው አባላት አስቀድመው ከፊል የመስክ ግምገማ ማድረግ የሚችሉበት ዕድል ቢኖር ጉብኝታቸውን የተሻለ ያደርግ እንደነበር ግልፅ ነው።

> ***በተለይ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከተፈጠረው የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም እና የምግብ ዋጋ ንረት ጋር ተያይዞ፣ የኢንዱስትሪው ፓርክ ሠራተኞች በምን ልክ ኑሯቸው እንደታወከ የቋሚ ኮሚቴው አባላት አስቀድመው ከፊል የመስክ ግምገማ ማድረግ የሚችሉበት ዕድል ቢኖር ጉብኝታቸውን የተሻለ ያደርግ እንደነበር ግልፅ ነው።***

ከዚኽ ባለፈም፣ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያያዞ፣ የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያን ተጠቃሚ ከነበረችበት፣ ከሰሃራ በታች ላሉት አገራት ከተሰጠው ከአፍሪካ ከቀረጥ ነፃ የንግድ ዕድል (አጎዋ) ማገዱ ይታወሳል። እንደሚታወቀው ይኽ ዕገዳ፣ በተለይም እንደ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪያል ያሉትን የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ክፉኛ ጎድቷቸዋል። ከዚኽ አኳያም፣ ፓርኩን የጎበኙት እንደራሴዎች ይኽ ዕገዳ በፓርኩ ሠራተኞች አኹናዊ የሥራ ኹኔታ ላይ ምን አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳደረገ እና ፓርኩም በዕገዳው ያጣቸውን የውጪ ምንዛሬን ጨምሮ፣ የሠራተኞችን ከሥራ ገበታቸው መባረር ጉዳይ ላይ በቂ ዳሰሳ ማድረግ እንደነበረበት ብሪጅ ያምናል። ከእነዚኽ ጉዳዮች በተጨማሪ፣ በአካባቢው ስላለው የድኅነት ወለል፣ ፣ የሠራተኞች የደመውዝ ገቢ ግብር ኹኔታ፣ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ስለሚደረገው መንግስታዊ ጥበቃ እና የኢንዱስትሪ ፓርኩ ሠራተኞች ስላሏቸው ተደራጅቶ መብታቸውን የመጠየቅ መብት ዝርዝር ትንተና ላይ የተመረኮዘ የመስክ ጉብኝቶች ሊደረግ ይገባ እንደነበርም ማስታወስ ያሻል። ከእነዚኽ ወሳኝ ጉዳዮች በተጨማሪም፣ እንደራሴዎቹ ለመስክ ጉብኝት በሚሄዱባቸው ወቅቶች ማብራርያ የሚሰጧቸውን ግለሰቦች እና ተቋማት እንዴት እና ለምን እንደሚመርጡ፣ ለመራጮቹ ግልፅ መሆን ይኖርበታል እንላለን። በፓርኩ የእንደራሴዎቹ የመስክ ምልከታ በኩል ያቀረብነው አጭር ምልከታ፣ ወደፊት በሌሎች ተቋማት ላይ የሚደረጉ ጉብኝቶች እነዚኽን መሰል የምክረ-ሐሳብ ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ ያካተቱ እንደሚሆኑም ተስፋ እናደርጋለን።

አጠር ያለውን ዳሰሳዊ ምልከታችንንን ለመጠቅለል ያህልም፣ እንደራሴዎቹ አኹን ባለው የምልከታ ሽፋናቸው ኹሉንም አዎንታዊ እና አሉታዊ ገፆችን በሙሉ መዳሰስ የሚያስችል አቅም ስለማይኖራቸው፣ ለፖሊሲ ግምገማ እና መሻሻል ሊያደርጉት የሚችሉትን አስተዋጽዖ መገደቡ አይቀርም። ያም ሆኖ ግን፣ ወደ ፌዴራልም ሆነ ክልላዊ ተቋማት ተኪደው የሚደረጉ የመስክ ምልከታዎች፣ ከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ከሚደረጉት የተለዩ ውጤቶች ስለሚኖራቸው የምልከታችውን አድማስ በማመጣጠን እና በማቀናጀት አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ፖሊሲዎችን እና ሕጎችን ለመቅረጽም ሆነ ለማሻሻል በቂ የመረጃ ግብዓት ይሰጣቸዋል የሚለው የብሪጅ ዕምነት ነው።



ጉብኝት በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ

# ምክረ-ሐሳቦች

ከእነዚኽ አጭር ዳሳሳዎች አንፃርም፣ ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን የሚከተሉትን የማሻሻያ ምክረ-ሐሳሳቦች ያቀርባል።

1. እንደራሴዎቹ፣ የተቋማት ቁጥጥር ሥራቸውን፣ እንዲኹም የፖሊሲ እና የሕግ ማውጣት ተፅኖዖዎቻቸውን ለማጎልበት የሚረዷቸው የተደራጁ የክትትል ማዕቀፎች ያስፈልጓቸዋል።ከዚኽ በተጨማሪም የሚያቀርቧቸውን የፖሊሲ፣ የአሰራር እና የሕግ ማሻሻያዎችን ሪፖርት ከማድረግ ባሻገር፣ ያቀርቧቸው እነዚኹ የአሰራር እና የሕግ ማሻሻያዎች በተግባር እንዲውሉ ተፅዕኖ በማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል እንላለን።

2. የኢፌዴሪ እንደራሴዎች፣ ከሚከውኗቸውመደበኛ የመስክ ምልከታዎች ባሻገር በርካታ ሐሳቦች ሊገኙባቸው የሚችሉትን የማኅበረሰብ ውይይቶች ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል እንላለን፤ ይኽን መሰሎቹ የውይይት መድረኮችም፣ የታችኛው ኅብረተሰብ ክፍል ድምጾች በፖሊሲ እና በሕግ ማሻሻያ አልያም ቀረጻ ውስጥ እንዲካተቱ ይረዳቸዋል፤ እንደ ብሪጅ ዕምነትም፣ እንደራሴዎቹ እኒህን ድምፆች በሚገባ በሚወጡም ሆኑ በሚሻሻሉ ሕግጋት ውስጥ ማካተት ይኖርባቸዋል።

3. የሕዝብ ተወካዮቹ፣ ማኅበራዊ ተጠያቂነትን ማስፈን የሚችሉ ፕሮጀክቶች እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ግልጽ ነው፤  ከዚኽ አንፃርም፣ በሕዝብ ተሳትፎ የሚገኙ ልማት ተኮር ግብረ-መልሶች፣ በየትኛውም የመንግሥት ዕርከን እና በሚመለከተው የኅብረተሰብ ክፍል መካከል ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና መተማመንን ማስፈን መቻላቸው ግልጽ ነው፤ ነገር ግን፣ ከዚኽ ባሻገር እንደራሴዎቹ፣ እነዚኽን ግብረ-መልሶች በፖሊሲ ቀረፃ እና በሕግ ማውጣት ሂደቶች ውስጥ ግብዐት እንዲሆኑ ማስቻል ይጠበቅባቸዋል እንላለን። ለዚኽም ከኦኣለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍም ሆኑ ቀጠና ተኮር ተቋማት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያሏቸውን አጋርነቶች ማጠናከር እንደሚያስፈልጋቸው ማስታወስ ያሻል።

እንደራሴዎቹ ያደረጓቸው የመስክ ምልከታዎች ዘርፈ ብዙ እንደመሆናቸው፣ የተለያዩ ዘርፎችን ወደ አንድ ማዕከል በማምጣት ለፖሊሲ ቀረፃ እና ለሕግ የማውጣት ሥራ ግብዐት በመሆን ያገለግላሉ። ከዚኽ የሚገኘውን ጥቅም እና የተወካዮች ተፅዕኖ በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግም፣ እንደራሴዎቹ ከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸውን ትስስሮሽ ማጎልበት፣ የፖሊሲ ቀረፃ እና ሕግ የማውጣት ተጽዕኗቸውን ማጠናከር፣ እንዲኹም ጠንካራ የሆነ የክትትል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋቸዋል ብለን እናምናለን፤ ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያውያን መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው በኩል፣ ተስፋ እና ስጋታቸውን ማንፀባረቅም ሆነ ለሰላም እና ለልማት በአንድነት መረባረብ የሚቻላቸው፣ ይኽ ሲሆን ብቻ ነውና!!

# እንደራሴ

**እንደራሴ በብረጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።**

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.